www.chilot.me

# የተሻሻለው የ1994 ዓ/ም

# የሶማሌ ክልል

# ሕገ-መንግስት

ሚያዝያ 1994ዓ/ም

ጅጅጋ

www.chilot.me

# የተሻሻለው የ1994 ዓ/ም የሶማሌ ክልል ሕገ-መንግሥት

## መግቢያ

እኛ የሶማሌ ሕዝብ በእኛና በሌሎች የአገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ላይ ተንሰራፍቶ የነበረው የጭቆና ሥርዓት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችንን አፍኖ፣ በተዛቡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎች በመተብተብ ለድህነትና ለኋላቀርነት ዳርጎን በገዛ ሀገራችን እንደ ሁለተኛ ዜጋ በመቆጠር የሰቆቃ ኑሮ እንድናሳልፍ ማድረጉን በመቃወምና በማያዳግም ሁኔታም መታረም እንዳለበት በማመን፣

መላ የአገራችን ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ለዘመናት ባካሄዱት አኩሪ ተጋድሎ የነበረው ኋላቀርነትና አፋኝ ሥርዓት ተገርስሶ አገራችን ኢትዮጵያ የግለሰቦችና የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ጨምሮ የሁሉም ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሙሉ የተከበሩባትና በአጠቃላይ የሕግ የበላይነት የሰፈነባት ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መሆኗ የጋራ እድገታችን መፋጠን ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብ፣

እኛም የሶማሌ ሕዝብ ለተፋጠነ ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ለዘላቂ ሰላምና ለዳበረ ዲሞክራሲ የምንበቃው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥትን መሠረት ያደረገ፣ ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘበና ለክልሉ ህዝቦች የተከበሩልንን ሕገ-መንግሥታዊ መብቶች ባልተሸራረፈ ሁኔታ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችለን የራሳችን ሕገ-መንግሥት ሲኖረን እንደሆነ አጥብቀን በማመን፣

ከዚህ በመነሳት በቀጥተኛ ተሳትፎአችንና በዲሞክራሲያዊ አግባብ ከመካከላችን መርጠን በላክናቸው የክልሉ ምክር ቤት ጉባኤ ተወካዮቻችን አማካኝነት እስካሁን ድረስ የሚሰራበትን ክልላዊ ሕገ-መንግሥት ሐምሌ 10 ቀን 1987 ዓ/ም ለመጀመሪያ ጊዜ መክረን ያፀደቅነው መሆኑን እያስታወስን፣ ይኸው በሥራ ላይ ያለው ሕገ-መንግሥታችን ግልጽ አሠራርን የሚከተል፣ ለመረጠው ህዝብ ተጠያቂ የሆነና ብቃት ያለው መንግሥታዊ አደረጃጀትን በሚያሳይ አግባብ ጥልቅ ክለሳ ተደርጎበትና የአርብቶ አደሩን የኑሮ መሠረት ባገናዘበ መልኩ ተሻሽሎ መውጣት የሚገባው መሆኑን በውል በመረዳት፣

www.chilot.me

እነሆ ዛሬ_____ቀን 1994 ዓ/ም በጅጅጋ ከተማ ባካሄደው የክልሉ ምክር ቤት አንደኛ መደበኛ ጉባኤ ለዚሁ አላማ በተሰየመ አካል ተረቅቆ በቀረበው የተሻሻለ ሕገ-መንግሥት ላይ መክረንና በዝርዝር ተወያይተን ሰነዱን በ_____ድምጽ አጽድቀነዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1
### የክልሉ መንግሥት ስያሜ

ይህ ሕገ-መንግሥት ዲሞክራሲያዊ አወቃቀርን ይደነግጋል፡፡

በዚህ መሠረት የተቋቋመው መንግሥት «የሶማሌ ክልላዊ መንግሥት» በሚል ስም ይጠራል፡፡

### አንቀጽ 2
### የሶማሌ ክልል ወሰን

1. የሶማሌ ክልል የሶማሌ ሕዝብና ሌሎች በሶማሌ ውስጥ ለመኖር የመረጡ ህዝቦች የሰፈሩበት የተያያዘ መልክአምድር ሆኖ፡-

   - በሰሜን ጅቡቲ፣ አፋርና ሶማሊያ
   - በደቡብ ኬንያ፣
   - በምሥራቅ ሶማሊያ፣
   - በምዕራብ ኦሮሚያ ናቸው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው እንዳለ ሆኖ የአከላለል ለውጦች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 48 በተደነገገው መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 3
### የክልሉ ሰንደቅ አላማ

የክልሉ ሰንደቅ አላማ ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሃል ነጭ፣ ከታች ቀይ፣ በስተግራ በኩል ባለሦስት መአዘን ውሃ ሰማያዊ ሆኖ በውሃ ሰማያዊ መደብ መሃል ላይ ባለ አምስት ጫፍ ነጭ ኮከብ ይኖረዋል፡፡

www.chilot.me

### አንቀጽ 4
### የክልሉ አርማ

የክልሉ መንግሥት የራሱ አርማ ይኖረዋል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

### አንቀጽ 5
### የክልሉ መዝሙር

የሶማሌ ክልል መዝሙር የሕገ-መንግሥቱን ዓላማዎች፣ የሕዝቡን ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋና የክልሉ ህዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር በዲሞክራሲ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት እንዲሁም የክልሉ ህዝብ የዕድገት ብሩህ ተስፋ የሚያንፀባርቅ ሆኖ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

### አንቀጽ 6
### የክልሉ የሥራ ቋንቋ

የክልሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ሶማልኛ ነው።

### አንቀጽ 7
### ርዕሰ ከተማ

የሶማሌ ክልል ርዕሰ ከተማ ጅጅጋ ነው።

### አንቀጽ 8
### የፆታ አገላለጽ

በዚህ ሕገ-መንግሥት ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

## ም ዕ ራ ፍ ሁ ለ ት

## የሕገ-መንግሥቱ መሠረታዊ መርሆዎች

### አንቀጽ 9
### የሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነት

1. የሶማሌ ህዝብ የክልሉ የበላይ ሥልጣን ባለቤት ነው።
2. የህዝቡ የሥልጣን የበላይነት የሚገለጸው በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸውና በቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካይነት ይሆናል።

www.chilot.me

## አንቀጽ 10
## የሕገ-መንግሥት የበላይነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. ይህ ህገ-መንግሥት የክልሉ የበላይ ሕግ ነው። ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር ወይም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሣኔ ከዚህ ሕገ-መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም።
2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ፣ የመንግሥት አካል፣ የፖለቲካ ድርጅት፣ ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ይህን ሕገ-መንግሥት የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው።
3. በዚህ ሕገ-መንግሥት ከተደነገገው ውጪ በማናቸውም አኳኋን የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነው።

## አንቀጽ 11
## ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

1. ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው።
2. የግለሰቦችና የህዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸው።

## አንቀጽ 12
## የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው።
2. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም።
3. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፣ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።

## አንቀጽ 13
## የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት

1. የክልሉ መንግሥት አሠራር ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት።
2. ሕዝቡ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ሊያነሳው ይችላል።
3. ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ወይም የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል።

www.chilot.me

# ምዕራፍ ሦስት
## መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች

### አንቀጽ 14
### ተፈፃሚነትና አተረጓጎም

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ መንግሥት የሕግ አውጪ፣ የሕግ አስፈፃሚ እና የዳኝነት አካሎች በዚህ ምዕራፍ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።
2. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩ መሠረታዊ የመብቶችና የነፃነቶች ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች፣ ስምምነቶችና አለም አቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ።

## ክፍል አንድ
## ሰብአዊ መብቶች

### አንቀጽ 15
### የህይወት፣ የአካል፣ ደህንነትና የነፃነት መብት

ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለው።

### አንቀጽ 16
### በሕይወት የመኖር መብት

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው። ማንኛውም ሰው በህግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም።

### አንቀጽ 17
### የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው።

www.chilot.me

## አንቀጽ 18
## የነፃነት መብት

1. በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጪ ማንኛውም ሰው ነፃነቱን አያጣም።
2. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርአት ውጪ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም።

## አንቀጽ 19
## ኢ-ሰብአዊ አያያዝ ስለመከልከሉ

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት ኢ-ሰብአዊ ከሆነ ወይም ክብሩን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በድጌታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም። ለማንኛውም አላማና ሁኔታ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው።
3. ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛውንም ሥራ እንዲሠራ ማድረግ የተከለከለ ነው።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 « በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት» የሚለው ሐረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም፣

   ሀ. ማንኛውም እስረኛ በእስራት ላይ ባለበት ጊዜ በህግ መሠረት እንዲሠራ የተወሰነውን ወይም በገደብ ከእስር ከተለቀቀበት ጊዜ የሚሠራውን ማንኛውም ሥራ፣
   ለ. ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትክ የሚሰጠውን አገልግሎት፣
   ሐ. የማህበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማንኛውንም አገልግሎት፣
   መ. በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው የሚፈጸመውን ማንኛውንም የኢኮኖሚና ማኅበራዊ የልማት ሥራ፣

## አንቀጽ 20
## የተያዙ ሰዎች መብት

1. ወንጀል ፈጽመዋል በመባል የተያዙ ሰዎች የቀረበባቸው ክስና ምክንያቶች በዝርዝር ወዲያውኑ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲነገራቸው መብት አላቸው።
2. የተያዙ ሰዎች ላለመናገር መብት አላቸው፣ የሚሰጡት ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብባቸው እንደሚችል መረዳት በሚችሉበት ቋንቋ እንደተያዘ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጣቸው መብት አላቸው።
3. የተያዙ ሰዎች በአርባ ስምንት ሰዓታት ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አላቸው። ይህም ጊዜ ሰዎቹ ከተያዙበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለመምጣት

www.chilot.me

አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም። ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረቡ በተጠረጠሩበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለመሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽላቸው መብት አላቸው።

4. የያዛቸው የፖሊስ መኮንን ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜው ገደብ ፍርድ ቤት በማቅረብ የተያዘበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነታቸውን እንዲያስከብርላቸው የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አላቸው። ሆኖም ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ በተጨማሪ ጊዜ ሲጠየቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቀድ ይችላል። የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ሲወስን ኃላፊ የሆኑት የሕግ አስከባሪ ባለሥልጣኖች ምርመራውን አጣርተው የተያዘው ሰው በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለውን መብት የሚያስከብር መሆን አለበት።
5. የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደዱም። በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።
6. የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው። ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል።

## <u>አንቀጽ 21</u>
## <u>የተከሰሱ ሰዎች መብት</u>

1. የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለህዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አላቸው። ሆኖም የተከራካሪዎቹን የግል ሕይወት፣ የህዝብን የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል።
2. ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና ክሱን በጽሑፍ የማግኘት መብት አላቸው።
3. በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር፣ በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው።
4. የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው።
5. በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አላቸው።
6. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤቱ በተሰጠባቸው ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው።
7. የፍርድ ሂደቱ በማይገባቸው ቋንቋ በሚካሄድበት ሁኔታ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጎምላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው።

www.chilot.me

## አንቀጽ 22
## በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት

1. በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብአዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አላቸው።
2. ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሃይማኖት አማካሪዎቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው እና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር ለመገናኘትና እንዲጎበኟቸውም እድል የማግኘት መብት አላቸው።

## አንቀጽ 23
## የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለ መሆኑ፣

1. ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም። እንዲሁም ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ ቢኖርም ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣ ህግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ህግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

## አንቀጽ 24
## በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛውም ሰው በወንጀል ህግና ሥነ ሥርዓት መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም።

## አንቀጽ 25
## የክብርና የመልካም ስም መብት

1. ማንኛውም ሰው ሰብአዊ ክብርና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው የራሱን ስብዕና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነፃ የማሳደግ መብት አለው።
3. ማንኛውም ሰው በማንኛውም ስፍራ በሰብአዊነቱ እውቅና የማግኘት መብት አለው።

www.chilot.me

## አንቀጽ 26
## የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፡፡ በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 27
## የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱ ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው፡፡ ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል፡፡
2. ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውና የሚጻጻፋቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም፡፡
3. የመንግሥት ባለሥልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው፡፡ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነት፣ የህዝብን ሰላም፣ ወንጀል ለመከላከል፣ ጤናንና የህዝብን የሞራል ሁኔታ በመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነት በማስከበር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም፡፡

## አንቀጽ 28
## የሃይማኖት፣ የእምነትና የአመለካከት ነፃነት፣

1. ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የህሊና እና የሃይማኖት ነፃነት አለው፡፡ ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል ፤ ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል፡፡
2. በፌዴራል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 90/2/ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸው የሃይማኖት ትምህርትንና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ፡፡
3. ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በሃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም፡፡
4. ወላጆችና ሌሎች ሕጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሠረት የሃይማኖታቸውንና የመልካም ሥነ ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው፡፡

www.chilot.me

5. ሃይማኖትንና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው የህዝቡን ደህንነት፣ ሰላምን፣ ጤናን፣ ትምህርትን፣ የህዝብን የሞራል ሁኔታ፣የሌሎች ዜጎችን መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች መንግሥት ከሃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 29
## በስብእና ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች

ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የአገሪቱ ሕጎች በሰው ልጆች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች የሰው ዘር የማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ መውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር ወይም ኢ-ሰብአዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈፀሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይገታገድም፡፡ በሕግ አውጪው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔዎች በምህረት ወይም በይቅርታ አይታለፍም፡፡

# ክፍል ሁለት
## ዲሞክራሲያዊ መብቶች

## አንቀጽ 30
## የአመለካከት እና ሃሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት

1. ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት ሃሳቡን የመግለጽ ነፃነት አለው፡፡ ይህ ነፃነት በክልሉ ውስጥም ሆነ ከክልሉ ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ወይም በህትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሃሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶች ያካትታል፡፡
3. የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙሀን እንዲሁም የሥነ-ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል፡፡ የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል፡፡
   ሀ. የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን፣
   ለ የህዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት እድልን፣
4. ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሃሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሰራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የህግ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡
5. በክልሉ መንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያለ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል፡፡

www.chilot.me

6. እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሃሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመውስተው በሚወጡ ህጎች ብቻ ይሆናል። የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ህጋዊ ገደቦች በእነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ። የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የሚከለከሉ ይሆናሉ።
7. ማንኛውም ሰው ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦችን ጥሶ ከተገኘ በህግ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል።

## አንቀጽ 31
## የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው። ከቤት ውጪ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በህዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በማካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና የህዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ሥርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ።
2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ፣ የጦርነት ቅስቀሳዎችን እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ህጎች መሠረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም።

## አንቀጽ 32
## የመደራጀት መብት

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም አላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም አግባብ ያለውን ህግ በመጣስ ወይም ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሕገ-ወጥ መንገድ ለማደፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ናቸው።

www.chilot.me

## አንቀጽ 33
## የመዘዋወር ነፃነት

በፌዴራል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 32 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ ወይም በሕጋዊ መንገድ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ሰው በፈለገው የክልሉ አካባቢ የመዘዋወር፣ የመኖሪያ ቤት የመመስረት፣ ሠርቶ የመኖር፣ ሃብት የማፍራትና የመያዝ እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ክልሉን የመልቀቅ ነፃነት አለው።

## አንቀጽ 34
## የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብት

1. በህግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመሥረት መብት አላቸው። በጋብቻ አፈጻጸም ፣ በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው። በፍቺም ጊዜ የልጆችን መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ የህግ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ።
2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ ይመሰረታል።
3. ቤተሰብ የኅብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው። ከኅብረተሰብና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው።
4. በህግ በተለይ በሚዘረዘረው መሠረት በሃይማኖት፣ በባህል የሕግ ሥርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈጸሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል።
5. ይህ ሕገ-መንግሥት የግልና የቤተሰብ ህግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖቶች ወይም በባህሎች ሕጎች መሠረት መዳኘትን አይከለክልም። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 35
## የሴቶች መብት

1. ሴቶች ይህ ህገ-መንግሥት ባረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።
2. ሴቶች በዚህ ሕገ-መንግሥት በተደነገገው መሠረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።
3. ሴቶች በበታችነት በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ቅርስ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ቅርስ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው። በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች አላማ በፖለቲካ፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግሥትና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው።

www.chilot.me

4. ሴቶች ከጎጂ ባህል ተጽዕኖ የመላቀቅ መብታቸውን መንግሥት ማስከበር አለበት። ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች፣ ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው።
5. ሀ. ሴቶች የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ ደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው። የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሰራውን ሥራ ሁኔታ የሴቷን ጤንነት፣ የህፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በህግ ይወሰናል።

   ለ. የወሊድ ፈቃድ በህግ በሚወሰነው መሠረት ከሙሉ ደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል።
6. ሴቶች በክልሉ የልማት ፖሊሲዎች፣ እቅድና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈፃፀም፣ በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ሃሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።
7. ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር ፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው። በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው። እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው።
8. ሴቶች የቅጥር፣ የሥራ ዕድገት፣ የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው። /በመንግሥት ወይም በግል ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሴቶች/።
9. ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣ መረጃና አቅም የማግኘት መብት አላቸው።

## አንቀጽ 36
## የሕፃናት መብት

1. ማንኛውም ሕፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት፣

   ሀ. በሕይወት የመኖር፣

   ለ. ስምና ዜግነት የማግኘት፣

   ሐ. ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅ የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣

   መ. ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርቱ፣ በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚደርሱ ሥራዎችን እንዲሰራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፣

   ሠ. በትምህርት ቤቶች ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ላይ ከሚፈጸም ወይም ከጭካኔና ኢ-ሰብአዊ

2. ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት።

www.chilot.me

3. ወጣት አጥፊዎች፣ በማረሚያ ወይም በማቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ፣ በመንግሥት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች፣ በመንግሥት ወይም በግል እጓለማውታን ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው።
4. ከጋብቻ ውጪ የተወለዱ ህፃናት በጋብቻ ከተወለዱ ሕፃናት ጋር እኩል መብት አላቸው።
5. መንግሥት ለእጓለ ማውታን ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል። በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ፣ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሰረቱ ያበረታታል፣

## አንቀጽ 37
## ፍትህ የማግኘት መብት

1. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተውን ውሣኔ ወይም ፍርድ፣
   ሀ. ማንኛውም ማህበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፣
   ለ. ማንኛውንም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድኑ አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ 38
## የመምረጥና የመመረጥ መብት

1. ማንኛውም የክልሉ ህዝብ በዘር፣ በቀለም፣ በብሄረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላል አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት፦
   ሀ. በቀጥታና በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካይነት በህዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ፣
   ለ. ዕድሜው 18 ዓመት ሲሞላ በሕግ መሰረት የመምረጥ፣
   ሐ. በማናቸውም የመንግሥት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ፣ ምርጫው ሁሉ አቀፍ፣ በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሰረተና በምስጢር ድምፅ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነፃነት የሚገልጽበትና ዋስትና የሚሰጥ መሆን አለበት።
2. በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሠራተኞች፣ በንግድ፣ በአሰሪዎችና በሙያ ማህበራት ለተሳትፎ ድርጅቱ የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ማንኛውም ሰው በፍላጎቱ አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን አለበት።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/2/ በተመለከቱት ድርጅቶች ውስጥ ለኃላፊነት በታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይፈጸማሉ።

www.chilot.me

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/2/ እና /3/ ድንጋጌዎች የህዝብን ጥቅም ሰፋ ባለ ሁኔታ የሚነኩ እስከሆነ ድረስ በህዝባዊ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 39
## የሶማሊ ብሔር ብሔራዊ መብቶች

የሶማሊ ብሔር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የሶማሊ ሕዝብ፡-

1. የራሱን ብሔራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርሱንና ታሪኩን የመንከባከብና የማበልፀግ እንዲሁም በቋንቋው የመጠቀም፣ ቋንቋውን የማሳደግና ባህሉን የመግለጽ መብት አለው፡፡
2. በራሱ መልክአ ምድራዊ ክልል ውስጥ የራሱን ጉዳይ በራሱ የማከናወንና ራሱን የማስተዳደር እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ውስጥ በነፃነትና እድልዎ በሌለበት ተገቢና ፍትሃዊ በሆነ አግባብ ውጤታማ ተሳትፎ ለማድረግ መብት አለው፡፡
3. ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት፣ በሰፈረበት መልክአ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብት አለው፡፡
4. የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በሥራ ላይ የሚውለው፡-

   ሀ. የመገንጠሉ ጥያቄ በክልሉ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ፣

   ለ. የክልሉ ምክር ቤት የመገንጠል ውሣኔ በደረሰው በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የፌዴራል መንግሥት ሕዝብ ውሣኔ ሲያደራጅ፣

   ሐ. የመገንጠሉ ጥያቄ በህዝበ ውሣኔው በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ፣

   መ. የፌዴራሉ መንግሥት ለክልሉ ምክር ቤት ሥልጣኑን ሲያስረክብ፣

   ሠ. በሕግ በሚወሰነው መሠረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው፡፡
5. በዚህ ሕገ-መንግሥት ውስጥ « የሶማሊ ብሔር ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ የሶማሊኛ ቋንቋ የሚናገሩ፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የሥነ-ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክአምድር የሚኖር ህብረተሰብ ነው፡፡

www.chilot.me

## አንቀጽ 40
## የንብረት መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል። ይህ መብት የህዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት በመያዝና በንብረቱ የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረቱን የመሸጥ፣ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል።
2. ለዚህ አንቀጽ አላማ « የግል ንብረት» ማለት ማንኛውም በክልሉና ከክልሉ ውጪ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ወይም ህጋዊ ሰውነት በህግ የተሰጣቸው አገር አቀፋዊ ወይም ክልላዊ ማህበራት ወይም አግባብ ባላቸው ሁኔታዎች በግን በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማኅበረሰቦች በጉልበታቸው መፍጠር ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው።
3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥና የማይለወጥ የክልሉ ህዝብ የጋራ ንብረት ነው።
4. የክልሉ አርብቶ አደሮች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነፃ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት አላቸው። ዝርዝር አፈፃፀሙ በህግ ይወሰናል።
5. በክልሉ የሚገኙ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
6. የመሬት ባለቤትነት የሕዝብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለግል ባለሀብቶች በህግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ያስከብርላቸዋል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
7. ማንም ሰው በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርሰው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው። ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሣት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሣ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል። ዝርዝር አፈፃፀሙ በህግ ይወሰናል።
8. የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለህዝቡ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል።

## አንቀጽ 41
## የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶች

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በክልሉ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት አለው።
2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያውን፣ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው።

www.chilot.me

3. የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄዱ ማህበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው፡፡
4. የክልሉ መንግሥት የውሃ፣ የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለህዝቡ በተለይ ለክልሉ አርብቶ አደር ሊጠቀምበት በሚችል መንገድ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል፡፡
5. የክልሉ አርብቶ አደሮችና አርሶ አደሮች የብድር አገልግሎት እንደዲሁም ለእንስሳት ሀብት ልማት ያመች ዘንድ መንገድ፣ ገበያ እንደዚሁም ሌሎች መሠረተ ልማቶች እንዲያገኙ ያመቻቻል፡፡
6. መንግሥት የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ህፃናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል፡፡
7. መንግሥት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፣ እንዲሁም በሚያካሂደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሥራ እድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ያወጣል፣ ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል፡፡
8. መንግሥት የክልሉ ነዋሪዎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት እድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
9. ለክልሉ አርብቶና አርሶ አደሮች በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸውንና ለብሔራዊ ሀብት ካደረጉት አስተዋጽኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ውጤቶቻቸው የማግኘት መብት አላቸው፡፡ የክልሉ መንግሥት የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችን በሚተልምበት ጊዜ በዚህ አላማና አርብቶ አደሩን መሠረት ባደረገ ሁኔታ መመራት አለበት፡፡
10. መንግሥት የባህልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ለሥነ ጥበባ ለስፖርት መስፋፋት አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

## አንቀጽ 42
## የሠራተኞች መብት

1. ሀ. የፋብሪካና አገልግሎት ሠራተኞች፣ ገበሬዎች የእርሻ ሠራተኞች፣ ሌሎች የገጠር ሠራተኞች፣ ከተወሰነ ኃላፊነት ደረጃ ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግሥት ሠራተኞች የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታቸውን ለማሻሻል በማህበር የመደራጀት መብት አላቸው፡፡ ይህ መብት የሠራተኛ ማህበራትንና ሌሎች ማኅበራትን የማደራጀት ከአሠሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል፡፡
   ለ. በንዑስ አንቀጽ/ሀ/ የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታቸውን የማሰማት መብት አላቸው፡፡
   ሐ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ እና /ለ/ መሠረት ዕውቅና ባገኙት መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በሕግ ይወስናሉ፡፡
   መ. ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

www.chilot.me

2. ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰአት እረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የህዝብ በዓላት፣ እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው።
3. እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ መሠረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት የሠራተኛ ማኅበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋሉ።

## አንቀጽ 43
## የልማት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች አካባቢያቸውን የመጠበቅና የማልማት የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።
2. የክልሉ ነዋሪዎች በክልሉ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማኅበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።
3. የልማት እንቅስቃሴ ዋና አላማ የክልሉን ነዋሪዎች እድገትና መሠረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት ይሆናል።

## አንቀጽ 44
## የአካባቢ ደህንነት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች ንፁህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው።
2. የክልሉ መንግሥት በሚያካሂዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ እርዳታ ወደሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው።

# ም ዕ ራ ፍ  አ ራ ት
# የክልሉ መንግሥት አደረጃጀትና የሥልጣን ክፍፍል

## አንቀጽ 45
## የክልሉ መስተዳድር እርከኖች

ክልሉ በቀበሌ፣ በወረዳ ወይም በከተማና በክልል ምክር ቤቶች የተዋቀረ ነው። ይሁን እንጂ የክልሉ ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የአስተዳደር እርከኖችን ሊያዋቅርና ሥልጣንና ተግባራቸውን በሕግ ሊወስን ይችላል።

www.chilot.me

## አንቀጽ 46
## የክልሉ መንግሥት የሥልጣን አካላት

1. የክልሉ መንግሥት ሕግ አውጪ አካል የክልሉ ምክር ቤት ሲሆን፣ እሱም የክልላዊ መንግሥቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ተጠሪነቱም ለወከለው ሕዝብ ነው።
2. የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል የክልሉ ካቢኔ ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።

## አንቀጽ 47
## የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ውስጥ በግልጽ ተለይተው ለፌዴራል መንግሥት ወይም ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሉ መንግሥት በጋራ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውጭ ያለ ማናቸውም ሥልጣንና ተግባር የክልሉ መንግሥት ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ክልላዊ መንግሥቱ፡-

   ሀ. የክልሉን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣

   ለ. የክልሉን ሕገ-መንግሥትና ሌሎች ሕጎችን ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣

   ሐ. የፌዴራሉ መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሠረት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል፣

   መ. ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያቋቁራል፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥትንና ይህንን ሕገ-መንግሥት ይጠብቃል፣ ይከላከላል፣

   ሠ. የክልሉን ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ሕግ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣ ይህን በሚያስፈጽምበት ጊዜ የሀገሪቱን የትምህርት፣ የሥልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፣

   ረ. የክልሉን ፖሊስ ኃይል ያደራጃል፣ ይመራል፣ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ይጠብቃል፣

   ሰ. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 28 እንደተጠበቀ ሆኖ በሕግ መሠረት ምህረት ወይም ይቅርታ ያደርጋል፣

   ሸ. ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ ግብርና ሌሎች ታክሶችን ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ የክልሉን በጀት ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፣ ያስተዳድራል፣

   ቀ. በክልሉ መንግሥት ሠራተኞችና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣

   በ. የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

www.chilot.me

ተ. የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣

ቸ. በክልሉ በግል ባለቤትነት ሥር ካሉ ቤቶችና ከሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ በክልል መንግሥቱ ባለቤትነት ሥር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ይሰበስባል፣

ኀ. በክልሉ መንግሥት ባለቤትነት ሥር በሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ፣ የሥራ ግብር፣የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ ይጥላል፣ ይሰበስባል፣

ነ. ከፌዴራል መንግሥት ጋር፡-

(i) በጋራ ከሚያቋቁሟቸው የልማት ድርጅቶች የሚገኘውን የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክስ በሕጉ መሠረት ይካፈላል፣

(ii) ከድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይና ከባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በህጉ መሠረት ይካፈላል፣

(iii) ከከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና ከማንኛውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች የሚገኘውን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በህጉ መሠረት ይካፈላል፣

ኘ. በክልል መስተዳድር አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

አ. ከደን የሚገኝ የሮያሊቲ ክፍያን ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

ከ. በክልሉ ውስጥ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጣል፣

# ም ዕ ራ ፍ አ ም ስ ት

## ስለ ክልል ምክር ቤት

### አንቀጽ 48

### ስለ ክልሉ ምክር ቤት አባላት

1. የክልሉ ምክር ቤት አባላት ሁሉ አቀፍ ነፃ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምጽ በሚስጥር በሚሰጥበት የምርጫ ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ፡፡
2. የክልሉ ምክር ቤት አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ፡፡
3. የክልሉ የምክር ቤት አባላት የመላው ክልሉ ሕዝብ ተወካዮች ናቸው፡፡ ተገዥነታቸውም፣

ሀ. ለሕገ-መንግሥቱ

ለ. ለህዝቡና

ሐ. ለራሳቸው ህሊና ብቻ ይሆናል፡፡

www.chilot.me

4. ማንኛውም የክልል ምክር ቤቱ አባል በምክር ቤቱ ስብሰባ በሚሰጠው ድምጽ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም፣ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም።

5.ማንኛውም የክልሉ ምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፣ በወንጀል አይከሰስም።

6.ማንኛውም የክልሉ ምክር ቤት አባል የመረጠው ህዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በህግ መሠረት ከምክር ቤት አባልነት ይወገዳል።

## አንቀጽ 49
## የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግስት መሠረት የክልሉ ሕግ አውጭ አካል ነው።
2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ምክር ቤት በክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ነው።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ. በዚህ ሕገ-መንግሥት መሠረት የፌዴራሉ ሕገ-መንግሥትና ሌሎች ሕጎችን የማይፃረሩ ልዩ ልዩ ሕጎችን ያወጣል።

ለ. የሕዝቡን ብዛት፣ የክልሉን ስፋትና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ግምት ውስጥ በማስገባት በክልሉ ውስጥ የአስተዳደር እርከኖችን ወይም የራስ በራስ አስተዳደራዊ አካባቢዎችን ያቋቁማል።

ሐ. የፌዴራል መንግሥት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ከሌሎች ክልላዊ መንግሥታት ጋር የሚደረገውን ስምምነት ያፀድቃል።

መ. ምክር ቤቱን የሚመሩ አፈ-ጉባዔና ምክትል አፈ-ጉባዔ ይመርጣል፣ ለምክር ቤቱ ሥራ የሚያስፈልጉትን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ይሰይማል።

ሠ. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ርዕሰ መስተዳድሩን በምርጫ ይሰይማል፣ በርዕሰ መስተዳድሩና አቅራቢነት የክልሉን ካቢኔ ምክር ቤት አባላት ሹመት ያፀድቃል፣

ረ. የኦዲትና የቁጥጥር አካል ያቋቁማል፣

ቀ. የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ለመጠበቅ የፀጥታና የፖሊስ ኃይል ያቋቁማል፣

በ. የክልሉን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ዕቅዶችን ያፀድቃል፣

ተ. የክልሉን መንግሥት የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ሕጎችን ያወጣል፣ የክልሉን በጀት ያፀድቃል፣

ቸ. የክልሉ በጀት የሚከፋፈልበትን ቀመር ይወስናል፣

ኀ. ለማኅበራዊ አገልግሎት መስፋፋትና ለኢኮኖሚያዊ ልማት መፋጠን አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣

www.chilot.me

ነ. በክልል ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት እና ዋና ኦዲተሩን ይሾማል፤

ኘ. ለክልሉ መንግሥት በተከለለው የገቢ ምንጭ ግብርና ታክስ ይጥላል፤

አ. የክልሉን የሠራተኛ አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎችን በተመለከተ ሕግ ያወጣል፤

ከ. የሀገሪቱን ሕገ-መንግሥት፣ አዋጆችና ሌሎች ሕጎችን በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ደንቦችን ያወጣል፤

ወ. የክልሉን ርዕሰ መስተዳድርና ሌሎች የክልሉን መንግሥት አካላት ባለሥልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፤ የክልሉ የካቢኔ ምክር ቤት አሠራርን ይመረምራል፤

## አንቀጽ 50
## ስለ ምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔና ምክትል አፈ-ጉባዔ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የክልሉ ምክር ቤት የራሱ አፈ-ጉባዔና ምክትል አፈ-ጉባዔ ይኖሩታል፤
2. አፈ-ጉባዔና ምክትል አፈ-ጉባዔው በዚህ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/መ/ መሠረት አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት/ድርጅቶች/ አቅራቢነት ከአባላቱ መካከል የሚሰየም ሆኖ አፈ-ጉባዔው ተጠሪነቱ የክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. የአፈ-ጉባዔው የሥራ ዘመን የክልሉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

## አንቀጽ 51
## የአፈ-ጉባዔው ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. የምክር ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፤ ይመራል፤
2. ምክር ቤቱን በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፤
3. የምክር ቤቱን ጽ/ቤት ያደራጃል፤ ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፤
4. ምክር ቤቱ በአባሎቹ ላይ እንዲወሰድ የወሰነውን የዲሲፒሊን እርምጃዎች ይፈጽማል፤
5. በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፤

## አንቀጽ 52
## የምክትል አፈ-ጉባዔው ሥልጣንና ተግባር

ምክትል አፈ-ጉባዔው ተጠሪነቱ ለአፈ-ጉባዔውና ለክልሉ ምክር ቤት ሆኖ:-

1. በአፈ-ጉባዔው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

www.chilot.me

2. አፈ-ጉባዔው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይቻልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤

## አንቀጽ 53
## ስለ ክልል ምክር ቤት ጽህፈት ቤት

1. የክልሉ ምክር ቤት የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል፤
2. የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር በህግ ይወሰናል፤

## አንቀጽ 54
## የክልል ምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የክልሉ ም/ቤት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤
2. የክልሉ ምክር ቤት አባላት የሥራ ዘመን ለአምስት ዓመት ነው። የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል፤ የቀድሞው የምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ውስጥ አዲሱ የክልሉ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፤
3. የክልሉ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ በማይኖርበት ወቅት አፈ-ጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሶስተኛ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ-ጉባዔው ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።
4. የምክር ቤቱ ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል፤ ሆኖም ስብሰባው በዝግ እንዲካሄድ በአባላቱ ወይም በክልሉ የካቢኔ ምክር ቤት ከተጠየቀና ከክልሉ ምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄውን ከደገፉት ዝግ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል።

## አንቀጽ 55
## የውሳኔ አሰጣጥና የአሰራር ሥነ-ሥርዓቶች

1. ከክልል ምክር ቤት አባላት መካከል ከሁለት ሦስተኛ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤
2. ማናቸውም ውሳኔ የሚተላለፈው በክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ በተገኙት አባላት አብላጫ ድምጽ ይሆናል፤
3. ምክር ቤቱ አሠራሩንና የህግ አወጣጥ ሂደቱን አስመልክቶ ዝርዝር ህጎችን ሊያወጣ ይችላል፤

## አንቀጽ 56
## የሀገር ሽማግሌዎችና የጎሳ መሪዎች ጉባኤን ስለማቋቋም

የሽማግሌዎችና የጎሳ መሪዎች ጉባኤ በዚህ ሕገ-መንግሥት ያቋቁማል፤ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፤

www.chilot.me

# ም ዕ ራ ፍ ስ ድ ስ ት
## የሕግ አስፈፃሚ አካል

### አንቀጽ 57
### የአስፈፃሚነት ሥልጣን

1. የክልላዊ መንግሥቱ ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ሥልጣን የተሰጠው ለመስተዳድሩ ርዕሰ መስተዳድርና ለክልሉ ካቢኔው ምክር ቤት ነው።
2. ርዕሰ መስተዳድሩና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነታቸው ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. የካቤኒው ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ተግባራቸው በጋራ ለሚሰጡት ውሳኔ ለሚፈጽሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

### አንቀጽ 58
### የክልሉ የካቢኔ ምክር ቤት አባላት

1. የክልሉ ካቤኒ ምክር ቤት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ፣ የአስፈፃሚ ቢሮዎች ኃላፊዎችና በሕግ በሚወሰነው መሠረት ሌሎች አባላት የሚገኙበት አካል ነው።
2. የክልሉ ኬቢኔ ምክር ቤት ሰብሳቢ ርዕሰ መስተዳድሩ ነው።
3. የክልሉ ካቢኔ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለመስተዳድሩ ርዕሰ መስተዳድርና ለክልል ምክር ቤት ነው።
4. የክልሉ ካቤኔ ምክር ቤት በሚወሰነው ውሳኔ ለክልል ምክር ቤት ተጠሪ ይሆናል፣

### አንቀጽ 59
### የክልሉ የካቢኔ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

በፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ካቢኔ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. በክልል ምክር ቤቱና በፌዴራሉ መንግሥት የወጡ ህጎችና የተሰጡ ውሳኔዎች በክልሉ ውስጥ በሥራ መተርጎማቸውን ያረጋግጣል፣
2. የክልል መስተዳድሩን አስፈፃሚ አካላትና ሌሎች ተቋማት አደረጃጀት ይወስናል፣ በክልል ምክር ቤቱ ተቀባይነት ሲኖረው በሥራ ላይ ያውላል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፣ ይመራል፣
3. የክልሉን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ለክልል ምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያውላል፣
4. በዚህ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀፍ 3/ለ/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ የመስተዳድርና የአስተዳደር እርከኖች አደረጃጀት አጥንቶ ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

www.chilot.me

5. የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፤ የሕግ ረቂቆችን ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲፀድቁም በሥራ ላይ ያውላል።
6. በክልሉ ውስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፤
7. ክልል ምክር ቤቱ በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦችን ያወጣል፤
8. የካቢኔ ም/ቤት አባላትን ከስራ ያግዳል፤
9. ምክር ቤቱና ርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

## አንቀጽ 60
## የርዕሰ መስተዳድሩ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. ርዕሰ መስተዳድሩ አብላጫ ድምጽ የፖለቲካ ድርጅት/ድርጅቶች/ አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሰየማል፤
2. በዚህ ሕገ-መንግሥት መሠረት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የርዕሰ መስተዳድሩ የሥራ ዘመን የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ነው።

## አንቀጽ 61
## ርዕሰ መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ርዕሰ መስተዳድሩ የክልል መስተዳድሩ ሥራ መሪና የካቢኔ ምክር ቤት ሰብሳቢ ነው።
2. ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ ርዕሰ መስተዳድሩ፡-
   ሀ/ የክልሉን የካቢኔ ምክር ቤት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ይወክላል፤
   ለ/ የክልሉ የካቢኔ ምክር ቤት ያወጣቸውን ፖሊሲዎች፤ ደንቦች፤ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈፃሚነት ይከታተላል።
   ሐ/ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ፤ ምክትል ፕሬዚዳንት፤ ዋና ኦዲተርና የክልሉን ካቢኔ ምክር ቤት አባላት ሹመት ለክልል ምክር ቤቱ አቅርቦ ያስጸድቃል፤
   መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/ሐ/ ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ምክር ቤት ሊሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜና ሁኔታ ከምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ በመለስ ያሉትን የካቢኔ አባላት በጊዜያዊነት መድቦ እስከሚቀጥለው የምክር ቤቱ ስብሰባ ያሰራል፤
   ሠ/ የክልሉን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ተቋማትና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/ሐ/ ሥር ከተዘረዘሩት ውጭ የሆኑ የክልል መሥሪያ ቤቶች፤ ኃላፊዎች ለክልሉ ካቢኔ ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል፤
   ረ/ የክልሉን ደህንነት ለማስጠበቅ፤ ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር የተቋቋሙትን የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤
   ሰ/ በክልሉ የሚገኙትን የበታች አርከኖች ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

www.chilot.me

ሸ/ ስለክልሉ ሁኔታ፣ በካቢኔ ምክር ቤት ስለተከናወኑት ተግባራትና ስለወደፊት ዕቅዶች ለክልሉ ምክር ቤት በየወቅቱ ሪፖርት ያቀርባል፤
ቀ/ በሕግ መሠረት ይቅርታ ይደረጋል፤
በ/ ሕገ-መንግሥቱን ያከብራል፤ ያስከብራል፤
ተ/ በክልል ምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

## አንቀጽ 62
## የምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ሹመቱ የሚፀድቅ ሆኖ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-
   ሀ/ በርዕሰ መስተዳድሩና በክልሉ የካቢኔ ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤
   ለ/ ርዕሰ መስተዳድሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤
2. የምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ ካቢኔ ምክር ቤት ነው፡፡

## አንቀጽ 63
## የርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት

1. ርዕሰ መስተዳድሩ በዚህ ሕገ-መንግሥት የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል፡፡
2. የርዕሰ መስተዳድሩ ጽህፈት ቤት የካቢኔ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት በመሆን ጭምር ያገለግላል፤
3. ጽህፈት ቤቱ በርዕሰ መስተዳድሩ በሚመደብ ፀሐፊ ይመራል፤
4. ፀሐፊው ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ ሆኖ፡-
   ሀ. ጽህፈት ቤቱን በሰው ኃይልና በቁሳቁስ ያደራጃል፤
   ለ. የመስተዳድሩን ሰነዶች በአግባቡ ይይዛል፤ ይጠብቃል፤
   ሐ. የካቢኔው ምክር ቤት ቃለ-ጉባዔ በማገባ መያዙን ያረጋግጣል፤
   መ. በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

## አንቀጽ 64
## ስለ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ተቋማት መቋቋም

የክልሉን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ሥራዎች የሚያከናውኑ፣ የሚያስተባብሩና የሚመሩ ቢሮዎች፣ ኮሚሽኖችና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ ይቋቋማሉ፤ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፤

www.chilot.me

# ምዕራፍ ሰባት
## ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀርና የዳኝነት ሥልጣን

### አንቀጽ 65
### ስለ ነፃ የዳኝነት አካል መቋቋም

1. በክልሉ ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ሕገ-መንግሥት ተቋቁሟል።
2. የዳኝነት ሥልጣን ከመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በሕግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጭ የሚያደርግና በሕግ የተደነገገውን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም።

### አንቀጽ 66
### ስለ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዳኝነት

1. በዚህ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የሃይማኖትና የባህል ፍርድ ቤቶች ሊቋቋሙ ወይም ዕውቅና ሊሰጣቸው ይችላል።
2. ይህ ሕገ-መንግሥት ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት እውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካላት በዚህ ህገ-መንግሥት እውቅና አግኝተው ይደራጃሉ።

### አንቀጽ 67
### የዳኝነት ሥልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።
2. በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸውም የመንግሥት አካል ባለሥልጣን ወይም ሌላ ተፅዕኖ ነፃ ነው።
3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ፤ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም።
4. ማንኛውም ዳኛ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በሕግ ከተወሰነው የጡረታ እድሜ ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከዳኝነት ሥራው አይነሳም፤
   ሀ. የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በዳኞች የዲሲፕሊን ሕግ መሠረት ጥፋት ፈጽሟል ወይም ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል አንሶታል ብሎ ሲወሰን ወይም፤
   ለ. በሕመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስንና፤
   ሐ. የጉባኤው ውሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ከግማሽ በላይ ድምጽ ሲፀድቅ፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት አንድን ዳኛ ከዳኝነት ሥራ የሚያስነሳው ጥፋት ፈጽሟል ብሎ ጉባኤው ካመነበት ጉዳዩ በክልሉ ምክር ቤት እስኪወሰን ድረስ ከዳኝነት ሥራው ይታገዳል።

www.chilot.me

6. የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም።

## አንቀጽ 68
## የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና ሥልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት አካል በጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በወረዳ ፍርድ ቤት ይደራጃል፣
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-
   ሀ. ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛውና የመጨረሻው የዳኝነት ሥልጣን፣
   ለ. በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣንና፣
   ሐ. ማንኛውም ክልላዊ ፍርድ ቤት የሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር የማየት ሥልጣን ይኖረዋል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።
3. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከክልላዊ ሥልጣኑ በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፣
4. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት በሚሰጠው ውሣኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል፣
5. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል፣
6. የወረዳ ፍርድ ቤት የክልሉ የበታችና የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል ነው።
7. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት አካላቱን የሚያስተዳድርበትን በጀት ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፣ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል፣
8. የክልሉ ጠቅላይና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በውክልና ለሚሰሩት ፌዴራላዊ የዳኝነት ተግባር ከፌዴራል መንግሥት የበጀት ማካካሻ ይሰጣቸዋል፣

## አንቀጽ 69
## ስለ ዳኞች አሿሿም

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት በክልሉ ፕሬዚዳንት አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፣
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደርና ጉባኤ አቅራቢነት በክልል ምክር ቤት ይሾማሉ፣
3. የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት ለክልል ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌዴራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በዕጩዎቹ ላይ ያለውን አስተያየት መጠየቅና የተሰጠውን አስተያየት ከራሱ መግለጫ ጋር ለክልሉ ምክር ቤት የማቅረብ

www.chilot.me
ኃላፊነት አለበት። ሆኖም የፌዴራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የተጠየቀውን አስተያየት በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የክልሉ ምክር ቤት የእጩ ዳኞቹን ሹመት ያፀድቃል።

## አንቀጽ 70
## ስለ ክልሉ ዳኞች አስተዳደርና ጉባዔ መቋቋም

1. በክልሉ ውስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምጽ የሚወከሉበት የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ይቋቋማል፣
2. የክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የጉባዔው ሰብሳቢ ይሆናል፣
3. የጉባኤው አባላት ዝርዝር እንዲሁም ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል፣

## አንቀጽ 71
## ሕገ-መንግሥቱን ስለመተርጎም

1. ሕገ-መንግሥታዊ ክርክር ውሣኔ የሚያገኘው ከየወረዳ ምክር ቤት በሚወከል አንድ አባል በሚሰየም የሕገ-መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሽን ይሆናል፣
2. ኮሚሽኑ የክልሉ ሕገ-መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በሚያቀርብለት የውሣኔ ሃሳብ ላይ መክሮ በ60 ቀናት ውስጥ ውሣኔ ይሰጣል፣
3. የኮሚሽኑ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፣
4. ኮሚሽኑ የራሱ ሰብሳቢና ፀሐፊ ከመካከሉ ይመርጣል። ለሥራው የሚያስፈልገውን የጽህፈት አገልግሎትና የፋይናንስ ድጋፉ ከክልል ምክር ቤት ያገኛል፣

## አንቀጽ 72
## የሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ

1. የክልሉ ሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በዚህ ሕገ-መንግሥት ተቋቁሟል።
2. የክልሉ ሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አሥራ አንድ አባላት ይኖሩታል። አባላቱም የሚከተሉት ናቸው።
   - ሀ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ............................ ሰብሳቢ
   - ለ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት.................. ምክትል ሰብሳቢ
   - ሐ. በክልል መስተዳድር ፕሬዚዳንት አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት የሚሾሙ በሙያ ብቃታቸውና በሥነ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የሕግ ባለሙያዎች............ አባላት
   - መ/ በአፈ-ጉባዔው አቅራቢነት ከክልል ምክር ቤት አባላት መካከል የሚሰየሙ ሦስት ተወካዮች........................................ አባላት

www.chilot.me

## አንቀጽ 73
## የአጣሪ ጉባዔው ሥልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሕገ-መንግሥቱን አከራካሪ ጉዳዮች የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል። በሚያደርገው ማጣራትም የክልሉን ሕገ-መንግሥት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጉዳዩ ላይ የውሣኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለሕገ-መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሽን ያቀርባል።
2. ጉባዔው በክልሉ መንግሥት አካላት የሚወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከዚህ ሕገ-መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ በሚናቸውም ሁኔታ ሲነሳና ጉዳዩ በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለጉዳዮች አማካኝነት ሲቀርብለት አጣርቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለኮሚሽኑ ያቀርባል።
3. የሕገ-መንግሥት ትርጉም ጥያቄ በፍርድ ቤቶች ሲነሣ ጉባዔው፦
   ሀ. የክልሉን ሕገ-መንግሥት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ወዲያውኑ ይመልሳል። ሆኖም በአጣሪ ጉባዔው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ማናቸውም ባለጉዳዩ ይህንኑ ቅሬታውን በጽሁፍ ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይችላል።
   ለ. የሕገ-መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ የውሳኔ ሃሳብ ለኮሚሽኑ ያቀርባል። የኮሚሽኑም ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

# ም ዕ ራ ፍ ስ ም ን ት
## ወረዳ አደረጃጀትና ሥልጣን

## አንቀጽ 74
## አደረጃጀት

- ወረዳ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል።
  1. የወረዳ ምክር ቤት፣
  2. የወረዳ ካቢኔ ምክር ቤት፣
  3. በዚህ ህግ መሠረት የተቋቋመ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል፣

## አንቀጽ 75
## የወረዳ ምክር ቤት

1. የወረዳ ምክር ቤት ከክልሉ ምክር ቤት በታች የሚደራጅ አካል ነው።
2. የወረዳው ምክር ቤት፦
   ሀ. በሥሩ ከተደራጁ ቀበሌዎች በሚወከሉ የህዝብ ተመራጮች የሚቋቋም ነው።

www.chilot.me

ለ. ከአባላቱ መካከል አሸናፊ በሆነው ወይም አብላጫ ድምጽ ባገኘው ወይም ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት የሚሰየሙ አፈ-ጉባዔና ምክትል አፈ-ጉባዔ ይኖሩታል።

ሐ. እንደአስፈላጊነቱ ጊዜያዊና ቋሚ ኮሚቴዎችን ሊያዋቅር ይችላል።

## አንቀጽ 76
## የወረዳ ምክር ቤት አባላት አመራረጥና ተጠሪነት

1. የወረዳ ምክር ቤት አባላት በወረዳው ውስጥ ከሚገኙት የቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በቀጥታ በህዝብ ይመረጣሉ።
2. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸው ህዝብ ይሆናል።

## አንቀጽ 77
## የወረዳ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ. የወረዳውን ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶችና አስተዳደራዊ የሥራ ዕቅዶችና ፕሮግራሞችን ረቂቅ መርምሮ ያፀድቃል፣

ለ. በወረዳው ውስጥ መሠረታዊ የእንስሳት ሀብት ልማት እና የግጦሽ ልማት በአጠቃላይ የግብርና ልማት ሥራዎች ወቅቱን ጠብቀው መካሄዳቸውንና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት መከናወኑን ይከታተላል፣

ሐ. ነዋሪው ህዝብ ለልማት ሥራ በስፋት የሚነሳሳበትንና የሚንቀሳቀስበትን አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፣ በተለይ አርብቶ አደሩን ወደ ተረጋጋ የኑሮ ሁኔታ ለማምጣትና የውሃና የግጦሽ አገልግሎት በአቅራቢያው ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ ያመቻቻል።

መ. የወረዳው ምክር ቤት የህዝቡን የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት መሆኑን ለማረጋገጥ በእቅድ አወጣጥ አፈፃፀምና ግምገማ ሂደት ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ያሳትፋል።

ሠ. ከአባላት መሀከል አፈ-ጉባዔና ምክትል አፈ- ጉባዔ ይመርጣል። ዋና አስተዳዳሪም ይሰይማል።

ረ. በዋናው አስተዳዳሪ የሚቀርቡለትን ምክትል አስተዳዳሪንና የሌሎች ኃላፊዎችን ሹመት ያፀድቃል።

ሸ. የራሱን የአሰራር ሥነ-ሥርዓት የሚወስን ውስጠ ደንብ ያወጣል።

ቀ. በህግ በተወሰነው መሠረት የመሬት መጠቀሚያ ታክስ፣ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብርና ሌሎች የአገልግሎት ታክሶችና ክፍያዎች መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል።

በ. ክልሉ ከሚመድበው በጀት ውጪ ያለውን የወረዳውን የገቢ ምንጭ

www.chilot.me

በአግባቡ ይጠቀማል፤ በጀቱንም መርምሮ ያፀድቃል፤ በክልል ም/ቤት የተመደበለትን በጠቅላላ በጀት እንደወረዳው ፍላጎት ቅደም ተከተል በማውጣት ይመድባል፤ አጠቃቀሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

ተ. አግባብ ያላቸውን የክልሉን መንግሥት አካላት አስተያየት በመጠየቅ ከወረዳው አስተዳደር ውጭ የሆኑ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ይሾማል፤

ቸ. የወረዳውን ሰላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያ በሥራ ላይ ያውላል፤

## አንቀጽ 78
## የወረዳ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ

1. አፈ-ጉባዔው ተጠሪነቱ ለወረዳው ም/ቤት ሆኖ ወቅቱን ጠብቆ ምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራትና ጉባዔውን የመምራት ኃላፊነት ይኖርበታል።
2. ሌሎች የአፈ-ጉባዔው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች የክልል ምክር ቤቱን አፈ-ጉባዔ አስመልክቶ በዚህ ሕገ-መንግሥት የተደነገጉት እንደአግባብነቱ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 79
## የወረዳ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባዔ

1. ምክትል አፈ-ጉባዔው በምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔ በወረዳው ም/ቤት ተለይተው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።
2. አፈ-ጉባዔው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤
3. ለወረዳው አፈ-ጉባዔና ለወረዳው ም/ቤት ይሆናል፤

## አንቀጽ 80
## የወረዳ ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የወረዳ ምክር ቤት በየሶስት ወሩ ይሰበሰባል፤
2. ከአባላቱ መካከል ከሁለት ሶስተኛ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል። ውሣኔ የሚተላለፈው በአብላጫ ድምጽ ይሆናል፤
3. የወረዳ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት አመት ይሆናል። የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፤
4. የወረዳ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል። ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ-ጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ከጠየቁ አፈ-ጉባዔው የምክር ቤቱን አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

www.chilot.me

## አንቀጽ 81
## የወረዳ ምክር ቤት ጽ/ቤት

የወረዳ ምክር ቤት ጽ/ቤት ሊኖረው ይችላል።

## አንቀጽ 82
## የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት

1. የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት የወረዳው ሊቀመንበር ምክትል ሊቀመንበር እንዲሁም በወረዳው ውስጥ የተቋቋሙ ዋና ዋና አስፈጻሚ የሴክተር መ/ቤቶች ኃላፊዎች የሚገኙበት አካል ነው።
2. ወረዳው የካቢኔ ምክር የወረዳው ሕግ አስፈጻሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለሊቀመንበሩና ወረዳው ምክር ቤት ነው።

## አንቀጽ 83
## የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ. የፌዴራልና የክልሉ መንግሥት ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ መመሪያዎች፣ እቅዶችና ፕሮግራሞች በወረዳ ውስጥ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
ለ. በወረዳው ውስጥ የሚገኙ አስፈፃሚ አካላትን በበላይነት ያስተባብራል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፣ ይመራል፣
ሐ. የወረዳውን ዓመታዊ በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፣ ለወረዳው ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣
መ. በሕግ መሠረት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ፣ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብርና ሌሎች ገቢዎችን ይሰበስባል፣ ተጨማሪ ገቢዎች ስለሚገኙበት ሁኔታ አጥንቶ ለወረዳው ምክር ቤት ለውሣኔ ያቀርባል፣
ሠ. የወረዳውን ሰላምና ፀጥታ ይጠብቃል፣ የወረዳውን የፀጥታና የፖሊስ አካላት ይመራል፣ ሥራቸውን ያስተባብራል፣
ረ. ህዝቡን ለልማት ሥራ በስፋት ያነሳሳል፣ የገጠር ልማትን ያፋጥናል፣ የተፈጥሮ ሀብትን ይጠብቃል፣ ያለማል፣ ይንከባከባል፣
ሰ. የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ እቅዶችን አዘጋጅቶ ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣
ሸ. በወረዳው ውስጥ መሰረታዊው የእንስሳት ሀብት ልማትና የግጦሽ ልማት በአጠቃላይ የግብርና ልማት ሥራዎች ወቅቱን ጠብቆ ያካሂዳል፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ልዩ ትኩረት ሰጥቶት ያከናውናል፣
ቀ. በወረዳው ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ቅርሳቅርስ አስገላጊው ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገለት ስለመሆኑ በቅርበት ይከታተላል፣
በ. በወረዳው ምክር ቤትና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች

www.chilot.me

ተግባራት ያከናውናል፤

3. የወረዳ ካቢኔ ምክር ቤት አባላት በመንግሥታዊ ሥልጣናቸው ለሚፈጽሙት ተግባርና ለሚያሳልፉት ውሳኔ በጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀጽ 84
## የወረዳ ሊቀመንበር አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ከወረዳው ምክር ቤት መካከል አሸናፊ በሆነው ወይም አብላጫ ድምጽ ባገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት በወረዳው ምክር ቤት ይሰየማል፤
2. በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የወረዳው አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን የወረዳው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

## አንቀጽ 85
## በወረዳው ሊቀመንበር ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳው ሊቀመንበር ተጠሪነት ለወረዳው ምክር ቤትና ለርዕሰ መስተዳድሩ ሆኖ የወረዳው አስተዳደር ሥራ መሪ ነው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪው፡-

   ሀ. የወረዳውን ካቢኔ ም/ቤት ይወክላል፤ ይሰበስባል፤ ይመራል፤

   ለ. የፌዴራልና የክልል መንግሥት ፖሊሲዎች፤ ህጎች፤ መመሪያዎችና ፕሮግራሞች በወረዳው ውስጥ ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

   ሐ. የወረዳውን ካቢኔ ምክር ቤት አባላት ልዩ ልዩ ተቋማትንና በሥሩ የሚገኙትን ቀበሌዎች ሥራ በበላይነት ያስተባብራል፤ ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

   መ. የወረዳው ማህበራዊ አገልግሎቶች የኢኮኖሚያዊ የልማት ፕሮግራሞች እና እቅዶች ወቅቱን ጠብቀው ማዘጋጀታቸውን ይቆጣጠራል፤ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

   ሠ. ምክትል አስተዳዳሪውን ጨምሮ የወረዳውን መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ለወረዳው ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል፤

   ረ. የወረዳውን ህግና ሥርዓት እንዲያስከብሩ የተቋቋሙትን የፀጥታ የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

   ሰ. ከወረዳው ምክር ቤት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

www.chilot.me

## አንቀጽ 86
## የወረዳ ምክትል ሊቀመንበር አሰያየም ሥልጣንና ተግባር

የወረዳው ምክትል ሊቀመንበር አቅራቢነት ሹመቱ በወረዳው ምክር ቤት የሚፀድቅ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. ከሊቀመንበሩና ለወረዳው ካቢኔ ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤
2. ሊቀመንበር በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤
3. የወረዳው ምክትል ሊቀመንበር ተጠሪነት ለወረዳው ሊቀመንበርና ለወረዳው ካቢኔ ምክር ቤት ነው።

## አንቀጽ 87
## የወረዳ መስተዳድር ጽህፈት ቤት

1. የወረዳ ካቢኔ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት በሊቀመንበሩ በሚመደብ አንድ የሥራ ኃላፊ ይመራል፤
2. በዚህ ሕገ-መንግሥት የርዕሰ መስተዳድሩ ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት በሚመለከት የተደነገጉት እንደ አግባብነታቸው ለወረዳው ካቢኔ ምክር ቤት ጽ/ቤትም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 88
## የከተማ ምክር ቤቶችን ስለማቋቋም

1. በክልሉ የሚገኙ ከተሞች የልማት እድገት ደረጃቸውን መሠረት ያደረገ የከተማ ምክር ቤት ይኖራቸዋል።
2. የከተማውን ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር እንዲሁም ከሌሎች የመንግሥት አካላት ጋር ያላቸውን ግንኙነት የዝርዝር ህግ ይወስናል።

# ም ዕ ራ ፍ ዘ ጠ ኝ
## የቀበሌ አደረጃጀትና ሥልጣን

## አንቀጽ 89
## አደረጃጀትና ሥልጣን

1. ቀበሌዎች በቋሚና በተንቀሳቃሽ ይቋቋማሉ፤ ተንቀሳቃሽ ህብረተሰብ ባለበት አካባቢ በጥናት የተደገፈ የህብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ይዋቀራል፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

www.chilot.me

2. የቀበሌ አስተዳደር የክልሉ የመጨረሻው መንግሥታዊ የመስተዳድር እርከን ሲሆን በዚህ ሕገ-መንግሥት መሰረት ተጠሪነቱ እንደሁኔታው ለታቀፈበት የከተማ ወይም የወረዳ መስተዳድር ነው። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
3. ቀበሌ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል።
   ሀ. የቀበሌ ምክር ቤት፣
   ለ. የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት፣
   ሐ. የማህበራዊ ፍርድ ቤትና

## አንቀጽ 90
## የቀበሌ ምክር ቤት

1. የቀበሌ ምክር ቤት የቀበሌው ነዋሪ ህዝብ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ነው።
2. የቀበሌ ምክር ቤት አባላት በቀጥታ በቀበሌው ነዋሪ ህዝብ የሚመረጡ ይሆናል፣
3. የምክር ቤቱ አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸው ህዝብ ነው።
4. የቀበሌ ምክር ቤት ተጠሪነቱ እንደሁኔታው ቀበሌው ለታቀፈበት የከተማ ምክር ቤት ወይም የወረዳ ምክር ቤት ይሆናል።

## አንቀጽ 91
## የቀበሌ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የቀበሌ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. የወረዳው ምክር ቤት የሚያወጣቸው ዕቅዶችን፣ መመሪያዎችን በሥራ ላይ እንደዋሉ ያረጋግጣል፣
2. ከቀበሌው በምክር ቤት አባላት መካከል የቀበሌውን አፈ-ጉባዔ፣ ምክትል አፈ-ጉባዔ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር በምርጫ ይሰይማል፣ የቀበሌውን የአስተዳደር ምክር ቤት ያደራጃል፣
3. በቀበሌው ሊቀመንበር ካቢኔ የሚቀርቡለትን የቀበሌውን ምክትል ሊቀመንበርና ልየማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኞችን ሹመት ያፀድቃል፣
4. በቀበሌው ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፣
5. የተፈጥሮ ሀብትን ልማትና እንክብካቤ ሥራ ይከታተላል፣

## አንቀጽ 92
## የቀበሌ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔና ምክትል አፈ-ጉባዔ

የቀበሌ ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል በሚመረጡ አፈ-ጉባዔ እና ምክትል አፈ-ጉባዔ ይመራል፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፣

www.chilot.me

## አንቀጽ 93
## የቀበሌው ካቢኔ ምክር ቤት አወቃቀር

1. የቀበሌ ካቢኔ ምክር ቤት የቀበሌው ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበርና በህግ የሚወሰኑ ሌሎች አባላት የሚገኙበት የበታች አስፈፃሚ አካል ነው፣
2. የቀበሌው መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነት ለቀበሌው ምክር ቤትና ለወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት ወይም እንደአስፈላጊነቱ የከተማ መስተዳድር ይሆናል።

## አንቀጽ 94
## የቀበሌ ካቢኔ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የቀበሌ ካቢኔ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣
   ሀ. የቀበሌ ካቢኔ ምክር ቤት፣ የልማት ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ይነድፋል፣ ለቀበሌው ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፣ የሥራ ላይም ያውላል፣
   ለ. የተፈጥሮ ሀብት፣ ጥበቃ፣ እንክብካቤና ልማት ሥራ እንዲካሄድ ያደርጋል፣ ህዝቡንም ለልማት ሥራ ያነሳሳል፣ ያስተባብራል፣
   ሐ. የገጠር ልማትን ያፋጥናል፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እንክብካቤና ልማት ሥራ እንዲካሄድ ያደርጋል፣
   መ. ለቀበሌው ምክር ቤት በየወቅቱ የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፣
   ሠ. በቀበሌው ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣

## አንቀጽ 95
## የቀበሌው ሊቀመንበር አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የቀበሌው ሊቀመንበር ከቀበሌው ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ ይሰየማል፣
2. በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የቀበሌ ሊቀመንበር የሥራ ዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ነው።

## አንቀጽ 96
## የቀበሌው ሊቀመንበር ሥልጣንና ተግባር

1. የቀበሌ ሊቀመንበር ተጠሪነቱ ለቀበሌው ምክር ቤትና እንደሁኔታው ቀበሌው የታቀፈበት ከተማ ወይም ወረዳ አስተዳደር ሆኖ የቀበሌው ተጠሪ፣ የአስተዳደሩ ስራ መሪና የካቢኔ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ነው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌው ሊቀመንበር ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

www.chilot.me

ሀ. የቀበሌውን ካቢኔ ምክር ቤት ይሰበስባል፣ ይመራል፣
ለ. የበላይ የሆኑት የአስተዳደር አካላት የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ዕቅዶች በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
ሐ. ምክትል ሊቀመንበሩን ጨምሮ የቀበሌውን መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ለቀበሌው ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፣
መ. እጩ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን ዝርዝር ለቀበሌው ምክር ቤት አቅርቦ ያሾማል፣

## አንቀጽ 97
## የቀበሌው ምክትል ሊቀመንበር ሥልጣንና ተግባር

የቀበሌው ምክትል ሊቀመንበር በቀበሌው ሊቀመንበር ተመርጦ ሹመቱ በቀበሌ ም/ቤት የሚጸድቅ ሆኖ፡-

1. በቀበሌው ሊቀመንበርና ካቢኔ ም/ቤቱ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣
2. የቀበሌው ሊቀመንበር በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣
3. የቀበሌው ምክትል ሊቀመንበር ተጠሪነቱ ለቀበሌው ሊቀመንበርና ለአስተዳደር ም/ቤቱ ነው፣

## አንቀጽ 98
## የቀበሌው ማህበራዊ ፍርድ ቤት

1. የቀበሌው ማህበራዊ ፍ/ቤት የቀበሌው ማህበራዊ የዳኝነት አካል ሆኖ በዚህ ህገ-መንግሥት ተቋቁሟል። ዝርዝሩ በህግ ይሰወናል።
2. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በዚህ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 91 ንዑስ አንቀጽ /3/ ሥር በተደነገገው መሠረት ይሾማሉ።
3. የማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኞች የሥር ዘመን በቀበሌው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

# ም ዕ ራ ፍ አ ስ ር
# የክልሉ ፖሊሲ ዓላማዎች

## አንቀጽ 99
## አላማዎች

1. ማንኛውም የመንግሥት አካል የፌዴራሉንና የክልሉን ሕገ-መንግሥት ፣ ሌሎች ሕጎችና ፖሊሲዎች በሥራ ላይ ሲያውል በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት ዓላማዎች ላይ መመስረት አለበት።
2. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ «መንግሥት ማለት» የሶማሌ ክልል መንግሥት ማለት ነው።

www.chilot.me

## አንቀጽ 100
## ፖለቲካ ነክ ዓላማዎች

1. መንግሥት በዲሞክራሲ መርሆዎች ላይ በመመስረት የሶማሌ ክልል ህዝብ በሁሉም ድረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን ሁኔታ የማመቻቼት ግዴታ አለበት፡፡
2. መንግሥት ከሌሎች ክልሎች ጋር እኩልነትን፤ ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 101
## ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች

1. መንግሥት ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች በክልሉ በተጠራቀመ እውቀትና ሀብት ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስ አለበት፡፡
2. የክልሉ ኢኮኖሚ በዋናነት የተመሰረተው በእንስሳት ሃብት በመሆኑ መንግሥት ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን ሲቀርጽ የአርብቶ አደሩን የኑሮ መሰረት በማሻሻል ወደ ተረጋጋ ኑሮ የሚመጣበትንና የመሰረተ ልማት ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ የማመቻቼት ኃላፊነት አለበት፡፡
3. የክልሉ ነዋሪዎች ጎሳዎች እኩል እድገት እንዲኖራቸው የማድረግና ሀብት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
4. የክልሉን ኢኮኖሚ ከሃገር አቀፍ ኢኮኖሚ ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ከፌዴራል መንግሥት አካላት ጋር ጥረት ያደርጋል፤
5. የክልሉ መንግሥት የግል ባለሀብቶች በክልሉ ልማት እንዲሳተፉ ያበረታታል፤ አስፈላጊውንም እገዛ ያደርጋል፤
6. መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በህዝብ ስም በይዞታው ሥር በማድረግ ለህዝቡ የጋራ ጥቅምና እድገት እንዲውል ማድረግ ግዴታ አለበት፤፤
7. የክልሉ ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ሲዘጋጁ ህዝቡ በየደረጃው እንዲሳተፍ ማድረግ አለበት፡፡ የህዝቡንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት፡፡
8. የህዝቡን እውቀት፤ ጉልበትና ገንዘብ በማቀናጀት ፈጣን ልማት የሚረጋገጥበትን መንገድ መቀየስ አለበት፡፡ ህዝቡ በክልሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና እንዲኖረው ማድረግ አለበት፡፡ ስለሆነም ህዝቡ እቅዶችና ፖሊሲዎችን በመደገፍ ብቻ ሳይሆን በመፈጸምና በመገምገም መሳተፍ አለበት፡፡
9. በኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች እኩል የሚሳተፉበትን ሁኔታ የማመቻቼት ኃላፊነት አለበት፡፡
10. የሰራተኛውን ሕዝብ ጤንነት፤ ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት፡፡
11. የክልሉ ኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት ካለበት ዝቅተኛ ደረጃ ለማውጣት ጥረት ያደርጋል፤

www.chilot.me

## አንቀጽ 102
## ማህበራዊ ነክ ዓላማዎች

1. የክልሉ መንግሥት የአገሪቱንና የክልሉ አቅም በፈቀደ መጠን የክልሉ ነዋሪዎችና ጎሳዎች የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁህ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማህበራዊ ዋስትና በተቀናጀ መልኩ እንዲኖር ያደርጋል፣
2. ትምህርት በማንኛውም ረገድ ከሃይማኖትና ከፖለቲካ አመለካከቶች ከባህላዊ ተፅዕኖዎች ነፃ በሆነ መንገድ መካሄድ አለበት።
3. የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋው ሲደርስም ለተጎጂው እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ አለበት።

## አንቀጽ 103
## ባህል ነክ ዓላማዎች

1. የክልሉ መንግሥት መሰረታዊ መብቶችንና ሰብዓዊ ክብርን፣ ዲሞክራሲንና ሕገ-መንግሥትን የማይቃረኑ ባህሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።
2. መንግሥት የክልሉን የተፈጥሮ ሃብቶችን፣ የህዝቡን ባህል፣ ቋንቋ፣ ታሪካዊ ቅርሶችን ለመጠበቅና ለማዳበር እንዲቻል ተቋማዊ እንቅስቃሴ የማድረግ ግዴታ አለበት፣
3. የክልሉ መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነ-ጥበብን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ አለበት።
4. የክልሉ መንግሥት ወጣቱን ትውልድ የመንከባከብ፣ በተሟላ ሥነ-ምግባት የማነጽ፣ ከሱስ ነፃ የሆነና በአካልም ሆነ በአዕምሮ ጠንክሮ ኃላፊነት የሚሸከም፣ ሀገሩን የሚወድና ለወገኑ የሚቆረቆር ብቁና በራሱ የሚተማመን ዜጋ ሆኖ እንዲያድግ ያላሰለሰ ጥረት የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## አንቀጽ 104
## የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች

1. መንግሥት ሁሉም የክልሉ ነዋሪ ንፁህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት አለበት፣
2. ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢውን ደህንነት የማያናጋ መሆን አለበት፣
3. የህዝብ የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ህዝቡ ሃሳቡን እንዲገልጽ መደረግ አለበት፣
4. መንግሥትና የክልሉ ህዝብ አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው። በተለይ በረሃማነትን ለመከላከልና ለመግታት መንግሥት አስፈላጊውን ሁሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

www.chilot.me

# ምዕራፍ አስራ አንድ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 105
### የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ

1. ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት እና የክልሉ ምክር ቤት በማይሰበሰብበት ጊዜ የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት የሚስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ያወጣል፣
2. የመስተዳድር ምክር ቤቱ የሚስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌውን አውጥቶ በሥራ ላይ ባዋለ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ አፈ-ጉባዔው የክልሉን ም/ቤት በአስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ ማስጸደቅ አለበት፣
3. የመስተዳድሩ ም/ቤት ያወጣው የአስቸኳ ጊዜ ድንጋጌ የክልሉ ም/ቤት ተቀባይነት ካገኘ ሊቆይ የሚችለው ለስድስት ወራት ብቻ ይሆናል። ሆኖም የክልሉ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲወስን የሚስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው በየአራት ወሩ ሊታደስ ይችላል፣
4. የመስተዳድሩ ምክር ቤትና የክልሉ ምክር ቤት በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ የሚያወጣቸው ድንጋጌዎችና የሚወስዱቸው እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ በዚህ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 15፣16፣18/1/፣ 21/1/፣ 25፣ 27/1/ እና 39 የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ መሆን የለባቸውም።

### አንቀጽ 106
### የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ

1. በክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በሚታወጅበት ወቅት የክልሉ ምክር ቤት አባላትና ከህግ ባለሙያዎች መርጦ የሚመደብባቸው ሰባት አባላት ያሉት የሚስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ ያቋቁማል። ቦርዱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በክልሉ ምክር ቤት በሚጸድቅበት ጊዜ ይቋቋማል።
2. የሚስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።
   ሀ. በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ምክንያት የታሰሩትን ግለሰቦች ስም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይፋ ማድረግና የታሰሩበትን ምክንያት መግለጽ፣
   ለ. በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ወቅት የሚወሰዱትን እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ ኢ-ሰብአዊ አለመሆናቸውን መቆጣጠር፣
   ሐ. በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ እርምጃዎች ኢ-ሰብአዊ ድርጊት የፈጸሙ ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ፣
   መ. ማናቸውም የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ እርምጃ ኢ-ሰብአዊ መሆኑን ሲያምንበት የመስተዳድሩ ፕሬዚዳንት ወይም የመስተዳድሩ ምክር ቤት እርምጃውን እንዲያስተካክል ሃሳብ መስጠት፣
   ሠ. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ እንዲቀጥል ለክልሉ ምክር ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ያለውን አስተያየት ማቅረብ፣

www.chilot.me

## አንቀጽ 107
## የክልሉ ዋና ኦዲተር

1. የክልሉ ዋና ኦዲተር በመስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማል፤
2. የክልሉ ዋና ኦዲተር የክልሉን ቢሮዎችና የሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሂሳቦችን በመቆጣጠር በክልሉ ምክር ቤት የተመደበው አመታዊ በጀት በበጀት አመቱ እንዲሰሩ ለተወሰኑ ሥራዎች በሚገባ መዋሉን ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፤
3. የክልሉ ዋና ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት ያስፀድቃል፤
4. የዋና ኦዲተር ተጠሪነት ለክልሉ ምክር ቤት ይሆናል፤
5. የዋናው ኦዲተር ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር በህግ ይወሰናል፤

## አንቀጽ 108
## የሕገ-መንግሥት መሻሻያ ሃሳብን ስለማመንጨት

የሕገ-መንግሥት መሻሻያ ሃሳብ፡-
1. በክልሉ ምክር ቤት አባላት አንድ ሦስተኛ ድምጽ ሲደገፍ ወይም፤
2. በክልሉ ካቢኔ የአብላጫ ድምጽ ውሳኔ ሲደገፍ ወይም፤
3. በክልሉ ውስጥ ካሉ የወረዳ ምክር ቤቶች በአንድ ሦስተኛው የተጠየቀ ከሆነ፤

## አንቀጽ 109
## ሕገ-መንግሥቱን ስለማሻሻል

1. የዚህ ሕገ-መንግሥት ምዕራፍ ሁለትና ሦስት ድንጋጌዎች በፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 105 ከተደነገገው ውጭ ሊሻሻሉ አይችሉም፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉት የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ብቻ ይሆናል።
   - የክልሉ ምክር ቤት አባላት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ሲያፀድቁት ነው።
3. ይህ ንዑስ አንቀጽና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት የቀረበውን ማሻሻል፡-
   - የክልሉ ምክር ቤት አባላት ሁለት ሦስተኛ ድምጽ ሲያጸድቁት ነው።

## አንቀጽ 110
## ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ሰነድ

የዚህ ሕገ-መንግሥት የሶማልኛ ቅጅ ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ሰነድ ነው።